**AMHARIC A1 – STANDARD LEVEL – PAPER 2**
**AMHARIQUE A1 – NIVEAU MOYEN – ÉPREUVE 2**
**AMHARE A1 – NIVEL MEDIO – PRUEBA 2**

Tuesday 11 May 2004 (morning)
Mardi 11 mai 2004 (matin)
Martes 11 de mayo de 2004 (mañana)

1 hour 30 minutes / 1 heure 30 minutes / 1 hora 30 minutos

---

INSTRUCTIONS TO CANDIDATES

- Do not open this examination paper until instructed to do so.
- Answer one essay question only. You must base your answer on at least two of the Part 3 works you have studied. You may include in your answer a discussion of a Part 2 work of the same genre if relevant. Answers which are not based on a discussion of at least two Part 3 works, will not score high marks.

INSTRUCTIONS DESTINÉES AUX CANDIDATS

- N'ouvrez pas cette épreuve avant d'y être autorisé(e).
- Traitez un sujet de composition. Vous devez baser votre réponse sur au moins deux des œuvres de la 3^e^ partie que vous avez étudiées. Le cas échéant, vous pouvez inclure dans votre réponse une discussion sur une œuvre du même genre littéraire étudiée dans la 2^e^ partie du programme. Les réponses qui ne sont pas basées sur au moins deux des œuvres de la 3^e^ partie n'obtiendront pas une note élevée.

INSTRUCCIONES PARA LOS ALUMNOS

- No abra esta prueba hasta que se lo autoricen.
- Elija un tema de redacción. Su respuesta deberá basarse en al menos dos de las obras estudiadas en la Parte 3. Se podrán hacer comentarios sobre una obra de la Parte 2 del mismo género, si fuera necesario. Las respuestas que no incluyan una discusión sobre al menos dos obras de la Parte 3 no recibirán notas altas.

*ከሚከተሉት በአንዱ ላይ ሀተታ ፃፍ(ፃፊ):: መልስህ በክፍል 3 ባጠናሀቸው (ባጠናሻቸው) ቢያንስ ሁለት ስራዎች ላይ መመስረት አለበት:: በክፍል ሁለት ስር ከሚገኝ አንድ ተመሳሳይ የስነጽሁፍ ዘርፍ ማጣቀሻ ማስገባት ይፈቀዳል:: በክፍል 3 ባጠናሀቸው (ባጠናሻቸው) ቢያንስ ሁለት ስራዎች ላይ ያልተመሰረተ መልስ ከፍተኛ ነጥብ አያስገኝም::*

**ድራማ**

**1. ተከታዩን**

(ሀ) ያጠናሃቸውን ቢያንስ ሁለት ስራዎች በመጥቀስ ምልልስ ለድራማ ያለውን ጠቀሜታ ግለጽ::

ወይም ቀጣዩን ምረጥ::

(ለ) አንድን የድራማ ገፀባህሪ እራሱ በሚናገረውና ሌሎች ስለሱ በሚናገሩት እናውቀዋለን:: ይህንን ሃሳብ ያጠናሃቸውን ሁለት ድራማዎች በማወዳደር ግለጽ::

**ረጅም ልቦለድ**

**2. ተከታዩን**

(ሀ) የልቦለድ መቼት ጊዜና ቦታ ያላቸውን ጠቀሜታ ያነበብካቸውን ቢያንስ ሁለት ስራዎች በማነፃፀር ግለጽ::

ወይም ቀጣዩን ምረጥ::

(ለ) ምልሰት በልቦለድ ውስጥ ያለውን ጠቀሜታ ግለጽ:: መልስህ ቢያንስ ያጠናሃቸውን ሁለት ስራዎች በምሳሌነት የሚያወዳድር ይሁን::

**ስነግጥም**

**3. ተከታዩን**

(ሀ) የገጣሚው ስሜትና አመለካከት በቃላት ምርጫውና በምስል አፈጣጠሩ ላይ ይንፀባረቃል:: ይህንን ሃሳብ ያጠናሃቸውን ሶስት ግጥሞች በመመርኮዝ ግለጽ::

ወይም ቀጣዩን ምረጥ::

(ለ) ገጣምያን ተፈጥሮን በየራሳቸው መንገድ ያቀርቡታል::ባነበብካቸው ቢያንስ ሁለት ግጥሞች ውስጥ ተፈጥሮ እንዴት እንደቀረበ አስረዳ::

**ስድንባብ**

4. ተከታዩን

(ሀ) የአንድ ስድ ጽሁፍ (ለምሳሌም ወግ) ዋና መሰረቱ ስለአንድ ጉዳይ እውነትን ማቅረብ መቻሉ ነው:: ይህ ሃሳብ ትክክለኛ መሆኑን ያጠናሃቸውን ቢያንስ ሁለት ስራዎች በማወዳደር አስረዳ::

ወይም ቀጣዩን ምረጥ::

(ለ) ከአጭር ልቦለድና ከረጅም ልቦለድ ውጭ ያለ ስድ ጽሁፍ (ለምሳሌም ወግ) በማንበብህ ስለ ህይወት ያለህ ግንዛቤ ተለውጥዋል? ፀሃፊዎቹ ግንዛቤህን ለመለወጥ ለምን እንደቻሉ ያነበብካቸውን ሁለት ስራዎች በመጥቀስ አስረዳ::

**አጭር ልቦለድ**

5. ተከታዩን

(ሀ) አጭር ልቦለድ ነጠላ ግብ ያለው ሲሆን ታሪኩን በጥድፊያ ያቀርባል:: ይህንን ሃሳብ ያጠናሃቸውን ቢያንስ ሁለት አጭር ልቦለዶች በማወዳደር ግለጽ::

ወይም ቀጣዩን ምረጥ::

(ለ) ማንኛውም አጭር ልቦለድ በአስደሳች ሁኔታ ማለቅ አለበት? መልስህ ቢያንስ ያጠናሃቸውን ቢያንስ ሁለት ስራዎች በምሳሌነት የሚያወዳድር ይሁን::

**6. ሁለገብ (አጠቃላይ)**

ከሚከተሉት አንዱን መርጠህ መልስ(ሽ)::

(ሀ) የስነጽሁፍ አንባብያን ደስታን የሚያገኙት ስነጽሁፍ ህይወትን ለማሳየት በመቻሉ ነው:: አብራራ::

ወይም

(ለ) ስነጽሁፍ እንቅስቃሴ ነው:: የስነጽሁፍ ታሪክ ጥሩ ታሪክ የሚሆነው አንድን የለውጥ እንቅስቃሴ ሲያቀርብ ነው:: ይህንን ሃሳብ ያጠናሃቸውን ሁለት ስራዎች በምሳሌነት በማወዳደር አብራራ::

ወይም

(ሐ) ደራሲው ከሌላው ሰው በተለየ አከባቢውን በሚገባ ማስተዋል አለበት:: ለምን? ያጠናሃቸውን ስራዎች በመጥቀስ ይህንን ሃሳብ አስረዳ::

ወይም

**(መ) ስነጽሁፍ ዋነኛ አላማው አንባቢው ስለአንድ ጉዳይ እንዲረዳና እንዲሰማው ማድረግ ነው:: ይህንን ሃሳብ በምሳሌ አብራራ::**

---